

የአማራ ትግል ፍኖተ ካርታ

ከባህርዳር እስከ አራት ኪሎ ያለው የትግል ጉዞ

በአንድ አማራ ንቅናቄ ተዘጋጅቶ የቀረበ ምዕራፍ ሦስት ሰነድ

ጥቅምት 29 2016

የአማራ የትግል ፍኖተ-ካርታ እና ከባህር ዳር እስከ አዲስ አበባ የሚደረግ የትግል ጉዞ

የአማራው ትግል በቂ በሚባል መነቃቃት ላይ ያለ እና ለውጥ በሚያመጣ መልኩ እየተንቀሳቀሰ ነው። ለዚህም አንድ አማራ ንቅናቄ እንደ አደረጃጀት ትግሉ መስመር የያዘ እና ለአማራው ህዝብ እርሾ ሆኖ ለመጪው ትውልድ የሚተርፍ እንዲሆን በማሰብ ይህንን ሠነድ ለማዘጋጀት ተገድዷል።

አንድ አማራ ንቅናቄ

ONE AMHARA

EMAIL: one_amhara@mail.com

Twitter: @one_amhara

YouTube: አንድ አማራ ሚዲያ (oneamharamedia)

ማውጫ

ክፍል አንድ 4
1. የአማራ ፋኖ በአንድ ዕዝ መምጣት አስፈላጊነት 4
1.1 የአማራ ፋኖ ዕዝ 4
1.2. የአማራ ፋኖ ሰብሳቢ ኮሚቴ 5
1.3 የአማራ ፋኖ ሸንጎ 5
2. የአማራ ፋኖ አመራሮች እንዴት መመረጥ አለበት 6
2.1 በትምህርት የገፋ 6
2. 2 በመከላከያ ውስጥ የነበረ የውጊያ ልምድ ያለው:- 6
2. 3 በእድሜ የሰከኑ 6
3. የፋኖ አደረጃጀት አወቃቀር ምን መምሰል አለበት 6
3.4.1. ወታደራዊ 7
3.4.2. ፖለቲካዊ አደረጃጀት 7
3.4.3. የህዝብ ግንኙነት 8
3.4.4. የፋይናንስ ተቋማት 8
3.4.5. የጤና ዘርፍ 8
3.4.6. የደህንነት አደረጃጀት 9
ክፍል ሁለት 10
4. የአማራው ትግል ማሳካት ያለበት 10
4.1. የህልውና አደጋን መቀልበስ :- 10
4. 2. የአማራን መሪ መፍጠር :- 10
5. የአማራ ህዝባዊ መንግስት አመሰራረት 10
5. 1. የወረዳ: ዞን እና ክልል መንግስት አመሰራረት 11
ክፍል ሶስት 13
6. የትግል ጉዞ ወደ አዲስ አበባ 13
6. 1. ትግል ስልጣን ሲሆን 13
6.2. የህግ ጉዳዮች 14
7. ጥንቃቄዎችና/ ስጋቶች 14
7.1 ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች:- 14
ማጠቃለያ 15

ክፍል አንድ

1. የአማራ ፋኖ በአንድ ዕዝ መምጣት አስፈላጊነት

በመላው አማራ የሚገኝን የፋኖ አደረጃጀት ወደ አንድ ዕዝ ወይንም Command ስር ማምጣት በተጠና እና በተናበበ መልኩ የጠላትን ሃይል በአጭር ጊዜ ለማንበርከክ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። የአብይ አህመድን ሰራዊት ከወልቃይት እስከ ሸዋ ከቤተ-አማራ እስከ ጎጃም በተመሳሳይ ጊዜ በማጥቃትና በመወጠር ግብዓተ-መሬቱን ማፋጠን ይቻላል። ከሜካናይዝድ እስከ አየር ሃይል ብሎም በመደበኛና ኮማንዶ ሰራዊት በአንድ አካባቢ ላይ በተናጥል ጫና በማድረስ ለሚታወቀው የአብይ አህመድ ሰራዊት በአጭር ጊዜ እንዲፍረከረክ በሁሉም አካባቢ ከደፈጣ እስከ ፊት-ለፊት ዉጊያ በማድረግ የResource አቅሙን በቀላሉ ማዳከም ይቻላል። ይህም ማለት ጠላትን በራስ ደረጃ በማዉረድ በመረጥነዉ ሜዳ ላይ ለመደምሰስ ይጠቅማል። ለዉጥ ፈጣሪ ኦፕሬሽኖችን ተግባራዊ ለማድረግ በተናበበ መልኩ የሚንቀሳቀስ ትግል እና ታጋይ ያስፈልጋል።

ይህንንም ለማሳካት የአንድ ዕዝ የትግል መስመር መፍጠር አስገዳጅ ነዉ። ይህ የማይሆን ከሆነ ግን የአብይ ሰራዊት አሸናፊ የሚሆንበትን መንገድ ማለትም የፋኖን ሃይል በተናጥል በመምታት በአጭር ጊዜ ያዳክመዋል ። ይህንንም ታሳቢ በማድረግ የትኛውም የፋኖ አደረጃጀት በጋራ ለመንቀሳቀስ ዳተኛ ከሆነ የጊዜ ጉዳይ እንጂ ለጠላት በሚመች መልኩ መሰለፉን ማወቅ ይኖርበታል።

የአንድ አማራ አደረጃጀት የአማራን ህዝባዊ ስነልቦና እና ውቅር በአግባቡ የተረዳ በመሆኑ ለአማራው በሚመጥን እና በሚበጅ መልኩ ይህን የአንድ ዕዝ መዋቅር በሶስት ንዑስ ክፍሎች አንደሚከተለው አቅርቧል።

1.1 የአማራ ፋኖ ዕዝ

ይህ ዕዝ የሚመሰረተው ከሁሉም ቀጠና ወይንም ወረዳ ላይ ያሉ የፋኖ አደረጃጀት አመራሮችን በአንድነት በማሰባሰብ የጋራ የOperation Command እንዲፈጥሩ በማድረግ ነው ። ይህ ሲደረግ ግን የሁሉንም አባል የፋኖ አደረጃጀቶች የዉስጥ አደረጃጀታዊ ነጻነት በማያሳጣ መልኩ መሆን አለበት። ይህም ማለት የገንዘብ አሰባሰቡን፣ የሰራዊት ምልመላ ፣ ስልጠናውን እና የአስተዳደር ነጻነቱን ባከበረ መልኩ ይሆናል። የዚህም አላማ በጠላት ላይ ለሚወሰዱ እርምጃዎች በጋራ ተወያይቶ ለመወሰን እና የትጥቅ ብሎም የሰራዊት ትብብርን ለማድረግ ብቻ ይሆናል ። የትኛውም የፋኖ አደረጃጀት በደስታ ይህንን የጋራ ዕዝ እንዲቀላቀል ያስችለዋል ምክንያቱም የአደረጃጀት ነጻነቱን የሚነካ ባለመሆኑ ነው።

ይህ ዕዝ ልክ እንደ ኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ውስጥ ያሉት የኮማንዶ ፣ የመደበኛ ጦር ፣ የመካናይዝድ እና የአየር ሃይል ክፍሎች እንደሚፈጥሩት አይነት ጥምረት ይሆናል። አንድ ሃይል ሆኖ ጠላትን መግጠሙ በአጭር ጊዜ ከማፍረክረክ አልፎ የአማራ የወደፊት መሪ የሆኑ ፋኖዎችን ለዓለምአቀፉ ማህበረሰብ እና ለመላው ኢትዮጵያዊያን የሚያስተዋውቅ ይሆናል ።

አደረጃጀቱ ከሩቅ ምስራቅ ፣ምዕራብ እና በምስራቅ አፍሪካ ካሉ ሃገራት ጋር የጋራ አጀንዳን ቀርፆ የድጋፍ እና የትብብር ሰንሰለት ለመዘርጋት ይጠቅማል። አደረጃጀቱ አሁን ላይ ላሉ እና ለወደፊት ለሚፈጠሩ የፋኖ አደረጃጀቶች በር የሚከፍትና አመራሮቹን አንድ ወንበር ፣ አንድ ድምጽ በሚባል ደረጃ እንዲወከሉ ያደርጋል። ይህም አግላይ ያልሆነ እና ሁሉንም የፋኖ አደረጃጀት በተመሳሳይ መስመር የሚያሰልፍ ይሆናል።

1.2. የአማራ ፋኖ ሰብሳቢ ኮሚቴ

ይህ አካል የፋኖ ዕዝን ለስብሰባ የሚጠራ የሚያወያይ በመሃከላቸው ያሉ ክፍተቶችን እና ችግሮችን የሚፈታ አደረጃጀት ይሆናል።
ለዚህም የራሱ መተዳደሪያ ደንብ ያለው ፣ በፋኖ እዝ አባላት የሚመረጡ ግለሰቦችን ያካተተ ይሆናል። ይህ አደረጃጀት እጅግ የተወሰነ ስራዎች ያሉት ይሆናል። በፋኖ ዕዝ ላይ ምንም አይነት የሃይል ሚዛን የሌለው ሲሆን ፣ አላማውም የማስተባበር እንዲሁም ወደ ዕዙ አዳዲስ ያልተካተቱ አደረጃጀቶችን የማምጣት ስራ ይሆናል።

1.3 የአማራ ፋኖ ሸንጎ

ይህ አደረጃጀት የወታደራዊ ፍርድ ቤት ጋር ተመሳሳይነት ያለው እንዲሁም በፋኖ አደረጃጀት ውስጥ የስነ ምግባር ጉድለት ብሎም ወንጀል ነክ ጉዳዮች ሲፈጸሙ ጊዜያዊ ፍርድ ቤት ሆኖ የሚያገለግል ይሆናል። በየወረዳው እና በቀጠና ሊቋቋም ይችላል ። ተከሳሾችም ፍትህ የሚያገኙበት ፣ በራሳቸውም ሆነ በወኪል የሚከራከሩበት እንዲሁም ፍርድ ከተፈረደባቸውም በኋላ የመጡበት የፋኖ አደረጃጀት ፍርዱን የሚያስፈፅም ይሆናል። አፈፃፀሙንም የአማራ ፋኖ ሸንጎ ይከታተላል።

1.3.1- በወልም ሆነ በግል በፋኖ አባላት አማካኝነት የሚፈፀሙ የሥነምግባር ጉድለቶችን እንደዚሁም በፋኖ አባላት መብት ላይ የሚፈፀሙ የመብት ጥሰቶችን ተመልክቶ ዳኝነት የሚሰጥ የፋኖ የፍርድ ሸንጎ ይቋቋማል።

1.3.2- የፋኖ የፍርድ ሸንጎ የሚቋቋመው በሁለት እርከን ሆኖ ....አባላት ያሉት አንድ የመጀመሪያ ደረጃ እና...አባላት ያሉት አንድ የይግባኝ ሰሚ የፋኖ የፍርድ ሸንጎ አደረጃጀት ይኖረዋል። ሸንጎዎቹ ውሣኔ የሚሰጡት በስምምነት ካልሆነም በድምፅ ብልጫ ነው።

1.3.3- ማናቸውም የሥነምግባር ጉድለት በመጀመሪያ የሚሰማው የፋኖ አባሉ በአባልነት በሚገኝበት አደረጃጀት ባለው የፋኖ የመጀመሪያ ደረጃ የፍርድ ሸንጎ ሆኖ፣ ፍርድ የተሰጠበት አባል በፍርዱ ላይ ይግባኝ ለማለት ከፈለገ ይግባኙ የሚቀርበው ለፋኖ የይግባኝ ሰሚ የፍርድ ሸንጎ ይሆናል።

1.3.4- የፋኖ የይግባኝ ሰሚ የፍርድ ሸንጎ ፍርዱን እስኪሰጥ ድረስ የመጀመሪያ ደረጃ የፋኖ የፍርድ ሸንጎ የሰጠው ውሣኔ ታግዶ ይቆያል። ሆኖም ግን የፋኖ የይግባኝ ሰሚ የፍርድ ሸንጎ ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል።

1.3.5- የፋኖ የፍርድ ሸንጎ ተመልክቶ ፍርድ የሚሰጥባቸውን ዝርዝር የሥነምግባር ጉድለቶች ምን እንደሆኑ፣ የፋኖ አደረጃጀት የዕዝ ምክር ቤት በመመሪያ አውጥቶ ለሁሉም ፋኖዎች ግልፅ አድርጎ ይደነግጋል።

1.3.6- በሥነምግባር ጥሰቶች እና ጉድለቶች ላይ ክስ የሚያቀርበው፣ ፋኖው አባል የሆነበት አደረጃጀት ኃላፊ ወይንም እሱ የወከለው ሰው ይሆናል። የፍርድ ሸንጎዎችን ፍርድ የሚያስፈጽመውም ይኸው ሰው ይሆናል።

1.3.7- ማንኛውም የፋኖ አባል መብቱ ተጥሷል ሲል ከላይ እንደተመለከተው በየእርከኑ ቅሬታውን ለፋኖ የፍርድ ሸንጎ የማቅረብና የማስወሰን መብት አለው። ፍርዱም ከላይ በተመለከተው ዓይነት ይፈፀምለታል።

2. የአማራ ፋኖ አመራሮች እንዴት መመረጥ አለበት

2.1 በትምህርት የገፋ

ማንኛውም የፋኖ አደረጃጀት ሃላፊ ወይም መሪ ሲሆን በትምህርት የገፋ ቢሆን ይመረጣል። ምክንያቱም ወደፊት የፖለቲካ ውክልና እና ውይይት ሲያስፈልግ ለመረዳት ወይም ለማስረዳት የፖለቲካ እውቀትና አቅም ያለው መሆኑ ለሚደረጉ የትኛውም አማራዊ ውክልናዎች ውጤታማ ሆኖ እንዲሰራ ይረዳዋል።

2. 2 በመከላከያ ውስጥ የነበረ የውጊያ ልምድ ያለው፦

ከዚህ በፊት በወታደርነት ብሎም በአዋጊነት ልምድ ያላቸውን መሪ ማድረግ በቀላሉ ውጤት ለማምጣት ያግዛል።

2. 3 በእድሜ የሰከኑ

በእድሜ ገፋ ያሉ ፋኖዎችን ከወጣት የፋኖ አመራሮች ጋር አጣምሮ ማምጣት ፣ የአመራሮችን የማመዛዘን እና የመወሰን አቅምን ይጨምራል።

3. የፋኖ አደረጃጀት አወቃቀር ምን መምሰል አለበት

3.1 የፋኖ አደረጃጀቶች በወረዳዎች ከተደራጁ በኋላ በቀጠናዎች መደራጀት ይኖርበታል ።

3.2 የፋኖ አደረጃጀቶች እምነት ከማይጣልባቸው ድርጅቶችም ሆነ ግለሰቦች ጋር ምንም አይነት እርዳታዎችን እና የትግል ሃሳቦችን መቀበል የለባቸውም። በግል ፍላጎታቸው ከሚፎካከሩ ድርጅቶች ጋር በምንም ሁኔታ አባል አለመሆን ፤ ምክንያቱም በህዝብ ዘንድ ተቀባይነትን ያሳጣል እንዲሁም ትግሉን ሊያኮላሽና ሊያዳክም ይችላል።

3.3 የታቀዱ አፕሬሽኖችን ከመደረጋቸው በፊት መረጃ ማውጣት በትግሉ ላይ ቀላል የማይባል አደጋ የሚያመጣ በመሆኑ ጥንቃቄ ያስፈልጋል። በተለይም የድምጽ መጠለፎች ወይም በሳተላይት አካባቢያቸው ሊጠና እንደሚችል በማሰብ ጥንቃቄ መደረግ አለበት። ቢቻል አስፈላጊ የሆኑ መልእክቶችን ድምፅ ቀድቶ መላላክ ከመጠለፍ ይከላከላል። የተቀዳውን የድምፅ ቅጂ ከደረሰ በኋላ የተላከለትም ላኪውም በሁለቱም ወገን ድምፅ ቅጂውን ማጥፋት ይኖርባቸዋል።

3. 4 የፋኖ አደረጃጀት የአማራ ወኪል ሃይል በመሆኑ እጅግ የተጠናከረ እና አለም አቀፋዊ አቋም ሊኖረው ይገባል። ለዚህም አደረጃጀቱ፦

3.4.1. ወታደራዊ
3.4.2. ፖለቲካዊ
3.4.3. የህዝብ ግንኙነት
3.4.4 የፋይናንስ ዘርፍ
3.4.5. የጤና ዘርፍ
3.4.6. የደህንነት ዘርፍ

እነዚህን ስድስት ዋና ዋና አካላት የያዘ አደረጃጀት መፍጠሩ የአማራውን ሃይል የጠንካራ አቋም ባለቤት ያደርገዋል።

3.4.1. ወታደራዊ

የአማራ ፋኖ በታሪክ ኢጋጣሚ የተገኘ አማራዊ ተቋም መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል። ይህ ለትውልድ የሚተላለፍ የአማራ ህዝብ ተቋም እንዲሆን በማሰብ ሁሉም አማራ መትጋት ይኖርበታል። ፋኖ ችግር እግሩን ሲሰድ ብቅ የሚል እና የሚታደግ ሃይል ብቻ ሳይሆን ችግሮች ዳግመኛ እንዳይፈጠሩ የሚያደርግ ሀይል መሆን አለበት። ይህን ህልም ለማሟላት የእስራኤልን የወታደራዊ አደረጃጀት መንገድ መከተል ይኖርበታል። የትኛውም እድሜው የደረሰ የአማራ ወጣት ከመደበኛ ወታደራዊ ስልጠና ጀምሮ የጦር አመራር ስልጠናዎችን ነፃ በወጣና በሚወጡ ቀጠናዎች መስጠት ይኖርበታል። የሰለጠነው ሀይል ቢቻል የታጠቀ፤ ካልቻለም ከጠላት ነጥቆ መታጠቅ የሚችል ሃይል መሆን አለበት። ሁሉም የፋኖ አደረጃጀት የሶስት ወር እና የስድስት ወር የስልጠና እቅድ አውጥቶ መንቀሳቀስ ይኖርበታል ለዚህም ብቁ የሆኑ አሰልጣኞችን በየወረዳው በማስገባት በግልፅም በህቡዕ ስልጠና መስጠት ይኖርባቸዋል።

3.4.2. ፖለቲካዊ አደረጃጀት

የፋኖ አባላት የአማራው የዛሬም የነገም መሪዎች መሆናቸው ታውቆ ካሁኑ በቂ የሚባል የፖለቲካ እና የታሪክ እንዲሁም የህግ ጥናቶችን መጀመር ይኖርባቸዋል። ለተማሩ የፋኖ አባላት ፕሮግራም አደራጅቶ መንቀሳቀስ ይኖርበታል። ይህም የፖለቲካ ንቃትና እውቀት ከመፍጠር ባለፈ የፖለቲካ አቋም ማስያዝ ላይ መሰራት ይኖርበታል። የአዲሱን የፋኖ ፖለቲካዊ ምልምል የአስተሳሰብ ነፃነት ኖሮት ውጤት አምጪ እንዲሆን በ1960ዎቹ እንደተደረገው አንጃ ማስያዝ አይኖርበትም። ዲሞክራሲ የሚወለደው ከህዝብ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ ለመመለስ በሚደረጉ ጥረቶች መሆናቸው መታወቅ ይኖርበታል። ለዚህም አዕምሮው ከአንድ አስተሳሰብ ጋር Dogmatic ወይንም ተቸንካሪ አስተሳሰብ ጋር የተሰፋ መሆን ስሌለበት ነው። የትኛውም የፖለቲካ ስልጠና የሚሰጥ አካል ሰልጣኙን የአንጃ ወይም የአንድ አቋም ተከታይ ማድረግ አይኖርበትም ፣ በተቻለ መጠን የፖለቲካ፣ የህግ እና የታሪክ ስልጠና መስጫ ጥራዞች ተመሳሳይና በሁሉም አካባቢ በአንድ አይነት ስሜት መሰጠት ይኖርበታል።

የአማራን ፖለቲካ ወክለው የሚወጡ ግለሰቦች በሚደረግላቸው የማንኛውም የሚዲያ መጠይቆች ላይ ህዝብን በጅምላ ከመፈርጅ መቆጠብ እንዲሁም ጥልቅ የፖለቲካ አረዳድ ሊኖራቸው ይገባል። ኢትዮጵያ ህብረ ብሔራዊ አገር መሆኗን በተቀበለና በአማራው ላይ የተሰሩ ፀረ-አማራዊ ትርክቶችን በሚቀለብስ መልኩ ወደ መሃል ፖለቲካም የሚመጣውም ከሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች ጋር በጋራ አገርን የሚያስቀጥል መሆኑን የሚያስገዝብ መሆን አለበት ። ኢጋር የሆኑ ሃይሎችን ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ ነው። ይህም ማለት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ ጠንካራ ተፅዕኖ መፍጠር ከሚችሉ ሃይሎች ጋር ግንኙነት በቶሎ መመስረት ያስፈልጋል ። የኢትዮጵያ ፖለቲካ በመሳሪያ አፈሙዝ የታጀበ በመሆኑ እንደ ሱማሌ፣ ጋምቤላ፣ አፋር እና ሲዳማ ካሉ በትጥቅ የተደራጁ ክልሎች ጋር ጥሩ የሚባል ግንኙነት መፍጠር ያስፈልጋል።

አሁን ላይ ተፅዕኖ ፈጣሪ ከሚባሉት ሃይሎች ውስጥ:-

1. አፋር
2. ሱማሌ፣
3. ሲዳማ፣
4. ጋምቤላ፣ እና ከመንግስት በተቃራኒ የቆሙ የኦሮሞ ሃይሎች ናቸው።

መንግስት ለመመስረት በሚደረገው ሂደት የሚሳተፉ በመሆናቸው ወደ አዲስ አበባ በሚደረገው የትግል ጉዞ ላይ እነዚህን ሃይሎች ማግለል ፖለቲካዊ ኪሳራ ከማምጣቱም ባሻገር ከመንግስት ጋር ተደርበው ሊታገሉን እና ዳግመኛ የከበባ ስሜት ውስጥ እንድንቀመጥ ሊያደርጉን ይችላሉ።

በህዝብ ግንኙነት በኩል በሚተላለፉ ሃሳቦች ላይ ይህንን መሰረታዊ የትግል መስመር የተረዳ እና የሚያንፀባርቅ መሆን ይኖርበታል። በተለይም የአማራውን የህልውና ጥያቄዎች ለማስመለስ ከወዲሁ ለሌሎች ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች አማራዊ ጥያቄዎችን ማለማመድ ያስፈልጋል።

3.4.2.ነ. ከክልሉ ውጪ ያለው አማራ ፖለቲካዊ ውክልና ልዩ ዞን ፣ ልዩ ወረዳ፣ ልዩ አስተዳደር ብሎም የከተማ አስተዳደር ካቢኔ የመጋራት አካል መሆኑ የብሔር ፌደራሊዝም የሚከተል ሃገር በመሆኑ ማንኛውም መብቶች እና ጥያቄዎች በድፍረት መራመድ ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም አማራውን የሀገር ባለቤት የማድረግ ትግል እየተደረገ በመሆኑ።

3.4.2.2. የማንነት እና የወሰን ጥያቀዎች ፡-

የአማራ ክልልየ ህዝባችንን በማይመጥን መልኩ የተደራጀ በመሆኑ ለህዝባችን በሚመጥን መልኩ በሁሉም አቅጣጫዎች ከአማራው የተወሰዱ የአማራው አስተዳደራዊ ወሰኖች የትግሉ አካል መሆናቸውን ማሳወቅ ያስፈልጋል።

3.4.2.3 ፍትህ ፡-

የአማራው ትግል የአማራን የዘር ጭፍጨፋ ለማስቆም የሚደረግ ትግል በመሆኑ በወንጀሉ የተሳተፉትን ሀይሎች ለፍትህ የማቅረብ ትግል መሆን ይኖርበታል። ይህም ማለት ከገዳይ ሀይል ጋር የሚደረግ የፍትህ ትግል እንጂ ድርድር እንደማይኖር በአቋም ደረጃ መያዝ ያስፈልጋል ።

3.4.3. የህዝብ ግንኙነት

ይህ አካል ፋኖን በአገር አቀፍም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ የሚወክል እና የፋኖን ገጽታ የሚያሳይ በመሆኑ እጅግ ጠንቃቃና ዲፕሎማቲክ መሆን ይኖርበታል። በአገር አቀፍ ጉዳዮች ላይ ከጸታዊ፣ ከእምነት እና ከሌሎች ብሔሮች ጋር ቅራኔ የሚፈጥር ንግግር ከማድረግ መቆጠብ ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም ፋኖ ብሔርተኛ ሃይል መሆኑን ማሳወቅ ይኖርበታል ፤ የሌሎችን ብሔርተኞች ሉአላዊነት ማክበሩን የሚያሳይበት መግለጫ ይሆናል። በአለም አቀፍ በሚደረጉ መግለጫዎች ላይ የአማራውን ፍትህ ማጣት፣ መከራ በሚያሳይ መልኩ የሚሰራ መሆን ይኖርበታል።

3.4.4. የፋይናንስ ተቋማት

አማራዊ የትግል መርጃ ተቋማትን ማበራከት አስፈላጊ ቢሆንም እነዚህ ተቋማት በትግሉ ላይ አደጋ እንዳያደርሱ፣ መሬት ባሉ አደረጃጀቶች ላይ ያላቸው ተጽእኖ አደጋ በማያደርስ ደረጃ መሆን አለበት። በሃገር ውስጥ ያለው ሃብት እጅግ ትልቅና አስፈላጊ መሆኑ ታስቦ ፤ በሁሉም ወረዳዎች ጠንካራ የሃብት ስብሰባ ማድረግ ይኖርበታል። የአማራ ፋኖ ያለውን የሚሰጥ በመሆኑ አገር ውስጥ ከአዲስ አበባ ጀምሮ ጠንካራ የሃብት ስብሰባ ማድረግ ያስፈልጋል። የብዙሃን መገናኛዎች የሚገኙ የአማራ ማህበራዊ አንቂዎች አገር ውስጥ ብሎም በውጪ ያለውን አማራ ልትግሉ የፋይናንስ ድጋፍ እንዲደረግ መወትወት እና ማስተባበር ይኖርባቸዋል።

3.4.5. የጤና ዘርፍ

የአማራ ህዝብ በከፍተኛ የጦርነት ጫና ላይ ያለ በመሆኑ የጤና ባለሙያዎች በከፍተኛ ቁጥር መሳተፍ ይኖርባቸዋል። በቅርቡ በጤናው ዘርፍ ተመርቀው ስራ ያላገኙ አማራዎች ወደ ትግል ሜዳው በመሳብ ለማህበረሰቡም ብሎም ለታጋዩ የጀርባ አጥንት ሆነው ማገልገል ይኖርባቸዋል። ከፍተኛ የሚባል የመድሃኒት እጥረቶች ስለሚያጋጥሙ ከአለም አቀፍ ድርጅቶች ጀምሮ እስከ ዲያስፖራ አደረጃጀቶች በትጋት የመድሃኒት አቅርቦት ማድረግ ይኖርባቸዋል። በተፈናቃዮች ጣቢያ ያሉ አማራዎችም የጤና እገዛ አስፈላጊ በመሆኑ በጤናው ዘርፍ ላይ ጠንካራ አደረጃጀት መፍጠር ያስፈልጋል። ብሎም ከቀይ መስቀል ወይም ቀይ ጨረቃ ተቋማት ጋር ጠንካራ ግንኙነት መፍጠር ይኖርበታል።

3.4.6. የደህንነት አደረጃጀት

አማራ የስለላ ድርጅት (አስድ) ይህ አደረጃጀት በብ/ጀ/ል አሳምነው ፅጌ ወቅት የተፀነሰ እና በጅምር የቀረ በመሆኑ ። የአደረጃጀት አባላቱም በልዩ ሃይል ብሎም ከአገር ውጭ ተበትነው የሚገኙ በመሆናቸው በፍጥነት እነዚህን ሃይሎች ያካተተ የደህንነት አደረጃጀት መመስረት ያስፈልጋል። ይህ አደረጃጀት በመላው ኢትዮጵያ እና በአለም አቀፍ ደረጃ የመረጃ ፍሰቱን በጥብቅ እንዲያንቀሳቅስ መደራጀት ይኖርበታል። ይህ አደረጃጀት የሰራዊት የስለላ አባላትን መልምሎ የትኛውንም ውጊያ ከመደረጉ በፊት የጠላትን እንቅስቃሴ ማጥናት ብሎም የጠላት አዋጊዎችን በደምብ የሚያጠና ቡድን ማዘጋጀት ይኖርበታል።

ክፍል ሁለት

4. የአማራው ትግል ማሳካት ያለበት

የአማራ ህዝብ ትግል ከባህርዳር እስከ አራት ኪሎ
የአማራው ትግል ዋና አላማው ሁለት ነገሮችን ማሳካት ነው።
1. የህልውና አደጋውን መቀልበስ
2. የአማራን መሪ መፍጠር

4.1. የህልውና አደጋን መቀልበስ ፦

ህልውና ላይ የተደቀነ አደጋ ማለት አንድ ማህበረሰብ እንደ ህዝብ እንዳይቀጥል በፕሮጀክት ደረጃ ይዞ የሚንቀሳቀስ ፋሽስታዊ ሃይል አለ ማለት ነው። የአማራን ህዝብ ለህልውና አደጋ የዳረገው ፋሽስታዊ የአብይ አህመድ ስርአት እስካልተገረሰሰ ድረስ መፍትሄ እንደማይመጣ እና የህልውና አደጋው መቀልበስ ዘላቂ እንዲሆን በዘር ማጥፋት የተሳተፉ አካላት በፍትህ አደባባይ መቅረብ ይኖርባቸዋል።

4. 2. የአማራን መሪ መፍጠር ፦

ባለፉት 50 አመታት አማራው መሪ የሌለው በመሆኑ በሁሉም አቅጣጫ ተከቦ እንዲጨፈጨፍ ሃብቱና ንብረቱ እንዲመዘበር ሆኗል። መሪ የሌለው ህዝብ በቀላሉ የሚበተንና ሰብሳቢ የሚያጣ በመሆኑ በትንሹም እንኳን የተደራጁ ሃይሎች እንዲያጠቁት ሆኗል። ለዚህም የጉምዝ አማጺ ሃይልን እንደ ማሳያ ማስቀመጥ ይቻላል። የአማራ መሪ ማለት የአማራ የትግል ጥያቄዎች ናቸው። የአማራ መሪ የሆኑት ጥያቄዎችን ለማስመለስ የሚደራጅ የትኛውም አካል የአማራ መሪ ይባላል። ነገር ግን መሪዎች በሁለት መንገድ የሚመረጡ ሲሆን፤ አንደኛው በፍትሃዊና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በትግል ጀግንነት የአማራን የአስተዳደር ወንበር በሚቆጣጠሩ ሃይሎች ነው። ባህርዳር የአማራ ክልል የፖለቲካ አስኳል ሲሆን በአማራ ክልል ከሚገኙ ተጽዕኖ መፍጠር ከሚያስችሉ ከተማዎች አንዱ ነው። ባህርዳር ሀገራዊ የፖለቲካ ጫና ማሳደር የሚችል ከተማ በመሆኑ በተመሳሳይ ሁሉም አየር ማረፊያ ያላቸው የአማራ ክልል ከተሞችንም መቆጣጠር ትግሉን በአጭር ጊዜ የአሸናፊነትን መንገድ እንዲይዝ ያደርገዋል።

ባህርዳርን መቆጣጠር የክልሉን ምክር ቤት ፣ የመገናኛ ብዙሃን ፣የአየር ሃይል እንዲሁም አየር ማረፊያውን ለመቆጣጠር ያስችላል። ባህርዳርን በመቆጣጠር ጊዜያዊ አማራዊ መንግስት በመመስረት የአማራን ክልል መገናኛ ብዙሃንን ተቆጣጥሮ የአማራን ህዝብ በክተት አዋጅ ወደ አዲስ አበባ ለሚደረገው የትግል ጉዞ ለማዘጋጀት ይጠቅማል። ለዚህም ከአንድ እስከ ሁለት ወራት የሚፈጅ ዝግጅት ብሎም ከለሎች ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ጋር ጥምረት አድርጎ ህብረ ብሔራዊ ትግል ለማድረግ በር ይከፍታል።

5. የአማራ ህዝባዊ መንግስት አመሰራረት

የአማራው የትግል ምዕራፍ መስመር እየያዘ በመምጣቱ ትግሉ የራሱ የሆነ ፍኖተ ካርታ ያስፈልገዋል። ትግል ፍኖተ ካርታ ወይም መዳረሻ ከሌለው በድርድር የሚቋጭ ይሆናል። የአማራው ትግል ለምሳሌ ከዚህ በፊት ከነበረው የኦሮማራ ጥምረት ጀምሮ ብዙ ድሎችን ቢያገኝም ፍኖተ ካርታ ያልነበረውና መዳረሻው ያልተቀመጠ በመሆኑ ትግሉ በቀላሉ መጠለፍ ችሏል አሁንም የተጀመረው ትግል ተመሳሳይ አደጋ እንዳይገጥመው ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ ይፈልጋል ለዚህም ትግሉ በፍኖተ ካርታ መቃኘት ይኖርበታል። ለዚህም በዘላቂነት መፍትሔው አማራዊ መንግሥት በመመስረት ህዝቡ የሚያምንበት

ወኪል መፍጠር ነው ። መሪ የሌለው ህዝብ መጨረሻው ለተጨማሪ እንግልትና መጥፋት የተጋለጠ መሆኑ ታምኖ መሪ መፍጠር ጊዜ የማይሰጠው መዳረሻ ነው።
አብዛኞች በአማራ ትግል መሪ ነን ብለው ቢያስቡም በስልጣን ላይ ሆኖ የማያስተዳድር ማንኛውም ታጋይ መሪ ሳይሆን ትክክለኛ መጠሪያው ታጋይ ወይም አታጋይ ይባላል። በአማራዊ አገላለፅም ፋኖ እንለዋለን። ስለዚህ የአማራ ህዝባዊ መንግሥት ለመመስረት ህዝቡን የሚወክሉ አባላት በመፍጠር የፍኖተ ካርታው አካል በመሆን ይህ ረቂቅ ተዘጋጅቷል።

የአማራ ክልል በብዙ ወረዳዎች የተዋቀረ በመሆኑ በነዚህ ወረዳዎችና የክልል ከተሞች ላይ ከፋኖና በትግሉ አስተዋፅኦ ካደረጉ አካላት ጋር በየወረዳው ህዝባዊ አስተዳደር መመስረት ያስፈልጋል። ይህም በመንግሥት ከሚገኙ ህግ አውጪ፣ ህግ ተርጓሚ ፣ ህግ አስፈፃሚ ውስጥ ህግ አውጪውን የሚተካ ይሆናል።
የአማራው ማህበረሰብ በመከራ ውስጥ የቆየ መሆኑ የትግሉን ሃይል እንደ አይኑ ብሌን ሊጠነቀቅለት ይገባል። ይኸውም ምንም አይነት ወንጀል በህዝብና በንብረት ላይ እንዳይፈፀም መጠበቅ ያስፈልጋል። የብአዴን ሃይሎች ህዝቡ በፋኖ ላይ ምሬት እንዲኖረው በማድረግ በህዝቡ ላይ ከግድያ ጀምሮ ብዙ ወንጀሎችን ስለሚሰሩ ይህንን በከፍተኛ ጥንቃቄ መከታተል ፣መጠበቅና መመከት ያስፈልጋል።

5. ነ. የወረዳ: ዞን እና ክልል መንግስት አመሰራረት

5.ነ.ነ. በአንድ ወረዳ ህዝባዊ መንግሥት የመመስረት አካሄድ:-
የወረዳውን ምክር ቤት ቁጥር ልክ የሚሆን የሰው ኃይል ከፋኖና ታማኝ ታጋዮች ፣ የእምነት አባቶች የተውጣጣ ጊዜያዊ መንግሥት ማቋቋም ቀዳሚ ሲሆን ለዚህም ህዝባዊ ውይይት በማድረግ ተመራጮችን ማቅረብ ለህዝቡም ማስተዋወቅ ይኖርበታል ይህም ምርጫ ፊርማ በማሰባሰብ የሚጠናቀቅ ሲሆን የተመረጠው ኃይል ተደጋጋሚ ውይይቶችንና ትውውቆችን በማድረግ የህዝቡን ችግር በመረዳት የአመራር ብቃቱን ማሳየት ይኖርበታል። የተሰበሰበው ፊርማ በመጨረሻ ፓርቲ ለመመስረት ስለሚያስፈልግ በአግባቡ ተሰንዶ መቀመጥ ይኖርበታል።
የህግ አስፈፃሚ ወይም ፀጥታ ዘርፍን ፋኖ ተቆጣጥሮ ማህበረሰቡን የትጥቅ አጠቃቀም እና ሌሎችን ወታደራዊ ስልጠናዎች በመስጠት ለቀጣይ ትግል የተዘጋጀ ወረዳ ማድረግ ይኖርበታል።
የፖሊስ አካላትን የተሃድሶ ስልጠና በመስጠት በላያቸው ላይ ተቆጣጣሪ በመመደብ ወደ መደበኛ ስራቸው እንዲገቡ ማድረግ።
ማንኛውንም ለጦርነት አቅሙ የሚፈቅድ አማራ ከስድስት ሳምንት ያልበለጠ ስልጠናዎችን መስጠት የፋኖ ትልቁ ድርሻ ይሆናል።
በአመራር ከህሎት አቅም ያላቸው የፋኖ አባላት የአስተዳደር ወንበር ይዘው የወረዳ ቢሮዎችን ከነፖሊስ ቢሮ መምራት ይኖርባቸዋል። ይህም የታጠቀ፣ ህዝባዊ ተቀባይነት ያለው ፣ ጠንካራ የፋኖ መንግሥት ያለበት ወረዳ መፍጠር ያስችለናል።

5.ነ.2. የዞን አማራዊ መንግስት አመሰራረት

በአማራ ክልል ነነ ዞኖች ሲኖሩ እነዚህ ዞኖች ተጠሪነታቸው ለክልሉ ነው። ይህ ዞን ስልጣኑ ከወረዳ የሚመነጭ በመሆኑ በእያንዳንዱ ዞን የሚገኙ ወረዳዎች ወኪሎቻቸውን በመላክ በዞን ለሚገኙ ቢሮዎች ተመራጮችን መልምሎ በመላክ በእያንዳንዱ ዞን ያሉ ቢሮዎችን የማስተዳደር ስራ የሚሰራ ይሆናል።
እያንዳንዱ ለዞን አስተዳደርነት የሚመጣ የወረዳ ወኪል የመጣበት ወረዳ ወኪል ስለመሆኑ ማረጋገጫ የሚሆን የተረጋገጠ ፊርማ ይዞ መምጣት ይኖርበታል። በአንድ ዞን ውስጥ ከታች የተቀመጡት ቢሮዎችን የሚያሟሉ የፋኖ፣ የመንግሥት አካላት በመተካት ለቦታው የሚመጥኑ እጩዎችን ማቅረብ ይኖርበታል።
የዞን አመራሩ በየወረዳው እየዞረ ውይይቶችንና ከማህበረሰቡ ጋር ትዉውቅ የሚያደርግ ይሆናል።
በዚህም የሃብት ስብሰባ በማካሄድ የክልሉን የበጀት ክፍተት ማስተካከልና ነፃ የህዝብ አገልግሎት

የሚሰጡ የወጣት አደረጃጀቶችን በመፍጠር በበጀት ማነስ ምክንያት የሚፈጠሩ ክፍተቶችን የሚሞላ አደረጃጀት መፍጠር ማህበረሰቡ ላይ የሚፈጠረውን ጫና ይቀንሳል።
እያንዳንዱ ወረዳ ይሄን ሃይል በማደራጀት ሃላፊነቱን መወጣት ይኖርበታል። ይህ የዞን አመራር በስሩ የሚገኙ ወረዳ አስተዳደሮች ተናበውና ተዋውቀው የሚሰሩበትን መንገድ በመፍጠር በየወረዳው የሚካሄደውን የፀጥታ ኃይል ግንባታና ስልጠና በትኩረት መደገፍ ይኖርበታል ምክንያቱም አዲስ ለሚፈጠረው የአማራ ህዝባዊ መንግሥት የጀርባ አጥንት ሆኖ የሚያግዝ በመሆኑ ነው።

1. የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ
2. የዞኑ ምክትል ዋና አስተዳዳሪ
3. የግብርና መምሪያ ኃላፊ
4. የንግድና ትራንስፖርት መምሪያ ኃላፊ
5. የኢንዱስትሪና ከተማ ልማት መምሪያ ኃላፊ
6. የገንዘብና ኢኮኖሚልማት መምሪያ ኃላፊ
7. የውሃ ሃብት ልማት መምሪያ ኃላፊ
8. የአካባቢ ጥበቃ፣የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መምሪያ ኃላፊ 9. የትምህርት መምሪያ ኃላፊ
10. የጤና ጥበቃ መምሪያ ኃላፊ
11. የፍትህ መምሪያ ኃላፊ
12. የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች መምሪያ ኃላፊ
13. የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ
14. የባህል፣ ቱሪዝምና ፖርኮች ልማት መምሪያ ኃላፊ
15. የሲቪል ሰርቪስ ጉዳዮች መምሪያ ኃላፊ
16. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ 17. የቴክኒክና ሙያ መምሪያ ኃላፊ

5.1.3. የክልል መንግስት አመሰራረት

የክልል ቢሮዎች የዞን ውጤቶች ሲሆኑ ሁሉም ዞን አቅም አለው የሚለውን አመራሩን ወደ ክልል መላክ ይኖርበታል። ለዚህም ከዞኑ ምክር ቤት ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ተመርጦ መምጣት አለበት፣ ይህም ተአማኒነት ያለው መንግሥት ለመመስረት ያግዛል። የክልል አመራርና ማዕከላዊ ኮሚቴ እንደተሟላ ከየወረዳው የተሰበሰቡ ፊርማዎችን ይዞ በይፋ አማራዊ መንግሥት ፓርቲ ይመሰረታል። ይህም ጠንካራ የወታደራዊ ክንፍ ይዞ መንግስት ይህናል።
ከዚህ በመቀጠል ለዓለምአቀፉ ማህበረሰብ የትውውቅ መግለጫዎችን በማውጣት ለሌላውም ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚኖረው ብሄር ብሄረሰብ በማብሰር ሁለተኛውን የትግል ምእራፍ የሚጀመር የአማራ ህዝባዊ መንግሥት ይሆናል።
የክልል ቢሮዎች በፓርቲው ማኒፌስቶ ከነመተዳደሪያ ደንቡ የሚዘጋጅ ይሆናል።

ክፍል ሶስት

6. የትግል ጉዞ ወደ አዲስ አበባ

ትግል መዳረሻው ሁለት ነው አንድ ህግ መሆን ሁለት ስልጣን መያዝ ነው። ሁለቱ አላማዎች ካልተሳኩ ትግሉ ግቡን አልመታም ማለት ነው ።

6. ነ. ትግል ስልጣን ሲሆን

የአማራው ትግል አዲስ አበባ ከመሄዱ በፊት ባህርዳር ላይ ሆኖ ጥምረት ከፈጠራቸው ሃይሎች ጋር በመሆን በፊት አውራሪነት ፋሽስታዊ ስርአቱን መገርሰስ ይኖርበታል። ለዚህም የመላውን ኢትዮጵያዊ ህዝብ ተቀባይነት ለማግኘት ህብረ ብሔራዊ ትግል ማድረጉ ይረዳዋል።

1. አፋር
2. ሱማሌ
3. ሲዳማ
4. ጋምቤላ
5. ወላይታና ሌሎች የደቡብ ሃይሎች እና ከመንግስት ጋር ተቃራኒ የሆኑ የኦሮሞ ሃይሎች ጋር የዚህ ህብረ ብሔራዊ ትግል አካል አድርጎ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። ለውጥ ማምጣት የሚችል የአማራ ሃይል በባህርዳር መቋቋሙን የሚመለከቱ ለለውጥ የተዘጋጁ ሃይሎች በቀላሉ ለመደራደርና ለሚመሰረተው የሽግግር መንግስት ግብዓት ማድረግ ይቻላል። በተጨማሪም ከአለም አቀፍና በምስራቅ አፍሪካ ካሉ ሃገራት ጋር ስምምነቶችን በማድረግ ትግሉን ማጠናከር ይቻላል።

የትግል መቋጫ ስልጣን ሲሆን ፤ የታገሉበትን ብረት አስቀምጦ ህዝብን በወንበር ላይ ሆኖ ለማስተዳደር ይጠቅማል። የታገሉ ሃይሎችን ወደ ስልጣን ማምጣት ትልቁ ጥቅሙ የህዝቡን ችግር ለመፍታት አቅምና ቅርበት ያላቸው በመሆኑ ነው። በለውጥ ማግስት ለሚፈጠሩ የፀጥታ ስጋቶች አይነተኛ መፍትሔው ፤ ታጋይን የሃይልና የስልጣን ባለቤት ማድረግ ነው።

በአዲስ አበባ ከፍተኛ የሆኑ ድርድሮች የሚደረጉ ሲሆን ፤ በድምጽ ብልጫ ወይም በሪፈረንደም የሚወሰኑትን በይደር በማቆየት አገሪቷ ላይ በፍጥነት ሰላም ሰፍኖ የተረጋጋ መንግስት እንዲኖር ጥረት መደረግ ይኖርበታል። ለዚህም ፍትህ አይነተኛ ሚናውን ይጫወታል። በደቡብ ፣ በምስራቅ እና በመካከለኛው ኢትዮጵያ የሚገኙ የመከላከያ ሰራዊት አባላት በካምፓቸው እንዲቀመጡ በማድረግ አመራሮቻቸውን ወደ አዲስ አበባ ሰብስቦ በወንጀል የተሳተፉትን በመቅጣት ፤በወንጀል ያልተሳተፉትን ከአሸናፊው ሃይል ጋር በማጣመር የሰላም እና መረጋጋት ኮማንድ ፖስት ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ለዚህም ከ3 ወር ያልበለጠ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በማውጣት የታጠቁ ሃይሎችን የፀጥታው አካል አድርጎ መንቀሳቀስ ይኖርበታል። ለህዝቡ በቀጥታ የሚተላለፉ ውይይቶችን የሰላም ሰባኪ ሰዎችን በመሰብሰብ ማህበረሰቡ የሰላም እና ደህንነት ስሜት እንዲሰማው ስራ መሰራት ይኖርበታል። የአማራ ህዝብ ቁጥር በትክክል ያልተቆጠረ በመሆኑ በሽግግር ወቅት የሚኖረው አደረጃጀት የመደበኛውን የመንግስት ስርአት በሙሉ መወከል የለበትም።

6.ነ. ነ. በሽግግር ወቅት እና ከሽግግር በፊት ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶች

ከሽግግር በፊት የተጠናከረ የአማራን አደረጃጀት የሚመለከተው የፋሽስቱ ስርአት ትግሉን ለማኮላሸት እና ስልጣኑን ለማስጠበቅ ሊጠቀማቸው የሚችላቸው መንገዶች

6.ነ.ነ.ነ. ትግሉን የህዝብ ለህዝብ ስሜት እንዲኖረው ሊያደርግ ይችላል ለምሳሌ በኦሮሞና በአማራ ህዝብ መሃከል

6.1.1.2. አንዳአንድ የአማራ አክቲቪስቶች በማህበራዊ ሚዲያ በስሜት በሚያስተላልፉት መልእክት የአማራን ትግል የአንድ ሃይማኖት ፣ቋንቋ እና ብሄር ጫና የሚፈጥር ስሜት በመፍጠር ከብሄር ብሄረሰቦች ተቃውሞ እንዲቀሰቀስ ሊጠቀምበት ይችላል።
6.1.1.3. የኮንፌዴሬሽን / የመገንጠል አጀንዳዎችን ሊያመጣ ይችላል።

ሶስቱንም ሁነቶች ታሳቢ ያደረገ ዝግጅት የአማራው ሀይል ማድረግ ይኖርበታል።
ሙሉ ዝርዝሩን በሌላ ጥራዝ ጉዳዩ በቀጥታ ለሚመለከታቸው ሀይሎች የአንድ አማራ ንቅናቄ የሚያደርስ ይሆናል።

6.2. የህግ ጉዳዮች

የትኛውም ትግል ግቡ ስልጣን አልያም ህግ ሲሆን ህግ ደግሞ በትግል የተገኘን ሰላም መዋቅራዊ በሆነ መንገድ ማስቀጠያ ነው።

7. ጥንቃቄዎችና/ ስጋቶች

7.1 ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች፦

ሁሉም ፋኖ ህዝቡን በመሳሪያ ብቻ ሳይሆን ወንበር ላይም ተቀምጦ ለማገልገል የሚታገል ስለሆነ የአስተዳደር እርከኑን በመቆጣጠር ፋኖ የስልጣንም ትግል እንደሚያደርግ በግልፅ ለህዝብ ማሳወቅ ይኖርበታል።

የፋኖ አደረጃጀት መሪዎች ከአማራ ህዝብ ጋር የሚኖራቸው ውይይቶች ፍጹም ህዝብን ብሎም ወጣቶችን ያከበረ መሆን ይኖርበታል። የአማራ ህዝብ ላለፉት 50 አመታት በመከራ የቆየ በመሆኑ እንደ አይን ብሌን ያህል መጠንቀቅ እና ማከበር ያስፈልጋል። ወታደራዊ ቋንቋዎችን በህዝባዊ ውይይቶች ላይ መጠቀም ህዝባችንን ስጋት ውስጥ ሊከት ስለሚችል ጥንቃቄ ያስፈልጋል።

በትግሉ ፍጻሜ የስልጣን ሽኩቻዎች እና አለመግባባቶች ሊፈጠሩ ስለሚችሉ ይህን ችግር ለመፍታት የተቋቋመ ሃይል ያስፈልጋል። ቀደም ብሎ የተጠቀሰው የፋኖ ሸንጎ ለዚህ ያገለግላል።

ማጠቃለያ

የአማራ ህዝብ በክልል ውስጥ ብሎም ከክልል ውጪ የሚኖር በመሆኑ ፤ ለሁለቱም አካባቢ የሚሆን ጊዜያዊም ሆነ ዘላቂ መፍትሔዎች በማበጀት ፤ መዋቅራዊ ጥበቃ መፍጠር ያስፈልጋል። መዋቅራዊ ጥበቃ ማለት የጸጥታ ሃይሎች ተብሎ መተርጎም ይኖርበታል። የፀጥታ ሃይል ማለት ደግሞ ህግ አስፈፃሚ ማለት ነው ። ህግ አስፈፃሚ አካላት ከህግ አውጪ እና ተርጓሚ ጋር ኢተነጣጣይ በመሆናቸው ሶስቱንም ማቀፍ የሚችለው መንግስት ሲመሰረት ብቻ ነው። ኢትዮጵያ የብሄር ፈደራሊዝም ስርአት ተከታይ በመሆኗ በብሄር የተወከለ መንግስት ለመንግስቱም አስተዳደራዊ ወሰን ይሰጠዋል። የአማራ ክልል አስተዳደራዊ ወሰን እና መንግስት መዋቅር ያለው ቢሆንም ፤ከክልሉ ውጪ ያለው የአማራ ህዝብ መዋቅራዊ ጥበቃ (ህግ አስፈፃሚ) የሌለው ስለሆነ፤ አገሪቷም በብሄር ተደራጅቶ መንግስት መመስረት ብሎም አስተዳደራዊ ወሰን ማግኘት ስለሚቻል፤ አማራው ከክልሉ ውጪ የልዩ ዞን ፣ልዩ ወረዳ ፣ልዩ አስተዳደር፣ የከተማና ቀበሌ ካቢኔ መጋራት ጥያቄዎች እስካልተመለሱ ድረስ የአማራ ህዝብ የሃገር ባለቤት አይሆንም። ይህን ለማድረግ የህዝብ ቆጠራ እጅግ አስፈላጊና ግዴታ ነው። ይህ እስኪሆን ድረስ ግን በተቻለ መልኩ የአማራውን ህዝብ የፖለቲካ ውክልና ባለቤት ማድረግ ያስፈልጋል። በኢትዮጵያ ያለው የመንግስት ስርዓት በወኪልም በቀጥታም የሚደረግ በመሆኑ የህግ ለውጦች ለማድረግ፤ መላው የአማራ ህዝብ በብሄሩ ተቆጥሮ እና በአግባቡ ተወክሎ መሆን ይኖርበታል። ይህ ባልተሟላበት ሁኔታ ወደ ህግ የማውጣት ሂደት ቢገባ በድርድር ሜዳው ላይ ተፎካካሪዎች በቀላሉ ጥቅማቸውን የሚያስጠብቁበት ይሆናል። ከዚህም ባለፈ ከአማራው ጋር ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸውን ብሄር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ተደራጅተው በቂ የድምፅ ባለቤት እንዲሆኑ መትጋት ያስፈልጋል። ምክንያቱም የድምር ውጤቶች በዴሞክራሲያዊ ሜዳዎች ላይ ከፍተኛ ሚና ስለሚኖራቸው ነው። ከህግ ለውጦች በፊት በቂ ውክልና እና የህዝብ ቆጠራ ብሎም አጋር ማሰባሰብ ያስፈልጋል። ከዚህ በዘለለ የሚደረግ የቸኮላ ውሳኔዎች የማይታረቁ ፍላጎቶች ወደፊት እንዲመጡ የሚያደርግ እንዲሁም የፍላጎቶች አለመጣጣም የአገር ብተናን ሊያስከትል ስለሚችል በጣም ጥንቃቄ ያስፈልጋል። የአማራው ብሔርተኝነት ላይ የተሰሩ ትርክቶች እጅግ አደገኛ መሆናቸውን ተገንዝቦ ጉዳታቸውም አገርን እስከማፍረስ የትግላችን ውጤትም የህዝባችን መበተን ሊሆን ስለሚችል እያንዳንዷን እንቅስቃሴያችንን በጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል።

ይህን ጥራዝ ተከትሎ ከሚወጣው (ምዕራፍ 4) ሰነድ ውጪ ሌሎች ጥራዞችን የአንድ አማራ ንቅናቄ የማያውቃቸው መሆናቸውን አንባቢው እንዲረዳ እንመክራለን። በዚህ ጥራዝ ማህበረሰቡ እንዲሰበሰብ ታስቦ ፍፁም ይፋዊ በሆነ መንገድ በአንድ አማራ ንቅናቄ የማህበራዊ ትስስር ገፆች አዲለቀቅ ተደርጎል::

ከባህርዳር እስከ አራት ኪሎ ያለው የትግል ጉዞ

አንድ አማራ ንቅናቄ

ONE AMHARA

EMAIL: one_amhara@mail.com

Twitter: @one_amhara

YouTube: አንድ አማራ ሚዲያ (oneamharamedia)

